## ምድብ አንድ (የሙዓለ ሕፃናት ተማሪዎች)
## 20 ኛ ሳምንት
## ጌታችን በውኃ ላይ ተራመደ

### የትምህርቱ ዓላማ
❖ ስለ ጌታችን በፈጸማቸው ተዓምራት መሠረት መማር፡፡

### ምንባብ
❖ ማቴ 14÷22-33

### መግቢያ
❖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ተዓምራት ፈጽሟል፡፡ ዛሬም ጌታችን በባሕር ላይ በመንዝ ያደረገውን ተዓምር እንማራለን፡፡

### ትምህርቱ፡-
❖ አንድ ቀን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ብዙ ሕዝብ አስተምሮና በተዓምራት መግቦ ከጨረሰ በኋላ አበው ሐዋርያት በጀልባ እንዲቀድሙት አዘዛቸው፡፡ ሐዋርያትም እንዳዘዛቸው ፈጸሙ፡፡

❖ ጌታችንም ሕዝቡን አሰናብቶ ሊጸልይ ወደ ተራራ ወጣ÷ እስኪመሽም በዚያ ነበር፡፡

❖ ደቀ መዛሙርቱ /ሐዋርያት/ ሲቀዝፉ በኃይለኛ ሞገድ ታንኳይቱ ተጨነቀች፡፡

❖ በሌሊበት ግን ጌታችን ማዕበል በሚያማታው ባሕር መካከል÷ በውሃው ላይ እየተረመደ ወደ ታንኳይቱ መጣ፡፡

❖ ደቀመዛሙርቱ ይሄን ባዩ ግዜም ምትሐት መስሎአቸው÷ ደንግጠው ጮኹ፡፡

❖ ጌታችንም ***"አይዞአችሁ÷ እኔ ነኝ፤ አትፍሩ"*** አላቸው፡፡

❖ ጴጥሮስም ***"ጌታ ሆይ አንተስ ከሆንህ በውኃው ላይ ወደ አንተ እንድመጣ እዘዘኝ"*** አለ ጌታም ***"ና"*** አለው፡፡

❖ ጴጥሮስም ከታኳይቱ ወጥቶ በውኃው ላይ መራመድ ከጀመረ በኋላ÷ መሐል ላይ ሲደርስ የንፋሱን ኃይል አይቶ ፈራ መስጠምም በጀመረ ጊዜ ***"ጌታ ሆይ አድነኝ"*** ብሎ ጮኸ፡፡

❖ ጌታችንና መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስም ***"አንተ እምነት የጎደለህ ስለምን ተጠራጠርህ"*** አለው፡፡ እጁንም ዘርግቶ ያዘና ከውሃው አወጣው፡፡

❖ ጌታችን ጴጥሮስን ይዞ ወደ ታንኳይቱ ከገባ በኋላም ንፋሱ ተወ÷ መናወጡ ጸጥ አለ፡፡

❖ ደቀመዛሙርቱም ***በእውነት የእግዚአብሔር ልጅነህ ብለው አመኑ ሰገዱለትም***፡

### ጥያቄዎች
1. ክርስቶስ በውሃው ላይ ሲራመድ ሲያዩት ደቀመዛሙርቱ ምን አሰቡ?
2. ቅዱስ ጴጥሮስ አይዞአችሁ የሚለውን የጌታችንን ድምፅ ሲሠማ ምን አለ?
3. ቅዱስ ጴጥሮስ በውኃው ላይ መራመድ ከጀመረ በኋላ ለምን ሠጠመ?
4. ጌታችን በታንኳ ውስጥ አብሮአቸው ሲሆን ሐዋርያቱ ምን አደረጉ?

### መዝሙር፡-
ተናገሩ ድንቅ ሥራውን መስክሩ
ተዓምሩን ለዓለም ንገሩ፡፡

# Jesus Walking on Water



ይቆየን።